የሰ/መ/ቁ. 37201

ታህሳስ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ማታዶር አዲስ ጎማ አክሲዮን ማህበር ጠበቃ ደረጀ ታፈሰወርቅ ቀርበዋል

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ኤልያስ በቀለ ቀርበዋል

2. አቶ ዲባባ ዎርዶፋ ቀርበዋል
3. አቶ ፍቅረሰላም ቦጋለ ቀርበዋል
4. አቶ ፍቃዱ ይመኑ አልቀረቡም
5. አቶ ዓለሙ ወነታ ወኪል አቶ ኤልያስ በቀለ ቀርበዋል
6. አቶ ዮሃንስ ንጋዬ ቀርበዋል
7. አቶ አዲሱ በቀለ ቀርበዋል
8. አቶ ካሳሁን እሸቱ አልቀረቡም
9. አቶ ደረጀ ወ/ሚካኤል ቀርበዋል
10. አቶ ሙሉነህ ካሣ ቀርበዋል
11. አቶ ዋቅቶላ በዳሳ ቀርበዋል
12. አቶ ተክለማርያም ባዩ ቀርበዋል
13. አቶ መለሰ ፋንታሁን ቀርበዋል
14. አቶ ጌትነት ቶፋ ቀርበዋል

ጉዳዩ ለምርመራ በተቀጠረው መሰረት ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተንበታል፣

## ፍ ር ድ

ክርክሩ በዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካቹ ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 60960 መጋቢት 15/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት በመጠየቁ ነው።

በአሁኑ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሾች እንዲሁም የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን የተከራከረ ሲሆን ስር ከሳሾቹ ጥቅምት 30/1999 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ያቀረቡት መሰረታዊ ይዘቱ በተከሳሽ ድርጅት በተለያዩ ጊዜያት ቅጥር በመፈፀም በወር ብር 288.66 (ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከስድሳ ስድስት ሣንቲም) እየተከፈለን ስንሰራ ከቆየን በኋላ ምንም አይነት ጥፋት ሳንፈፅም ጥቅምት 21/1999 ዓ.ም አላግባብ ከሥራ ስላሰናበተን ውዝፍ ደሞዛችን ከፍሎ ወደ ስራችን ይመልሰን ይህ ካልሆነ ግን የስንብት ክፍያ የማስጠንቀቂያ ክፍያ፣ ካሳ፣ ክፍያ ለዘገየበት እንዲሁም ከበቂ ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍለን ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ስር ተከሳሹ በበኩሉ ታህሳስ 20/1999 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሰጠ ሲሆን፣ ይዘቱም የተጫኑ ጎማዎች እንዲያራግፉ ጥቅምት 19 ቀን 1999 ዓ.ም በቅርብ ኃላፊያቸው ሲታዘዙ በአድማ መልክ ተደራጅተው አናራግፍም እንዳሉና በማግስቱም ይህ እምቢተኝነታቸው በመቀጠሉ በህብረት ስምምነቱ አንቀፅ 4.4 ተራ ቁጥር 5 መሰረት ከስራ ሊሰናበቱ ችለዋል፤ የከሳሾቹ የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ስላልሆነ የሚከፈላቸው ክፍያ የለም ተብሎ ክሳቸው ውድቅ ይሁንልኝ የሚል ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም በግራ ቀኙ ወገኞች መካከል የቃል ክርክር አካሂዷል፤ የግራ ቀኙ ወገኖች ምስክሮችም ሰምቷል፤ የተገኘው ውጤትም ከሳሾቹ ጎማውን አናራግፍም ያሉት እሁድ እለት እንደነበርና በዚሁ ጊዜም በተቋሙ ውስጥ በተፈጠረው የስራ ጫና ምክንያት የትርፍ ሰዓት ክፍያ እየተከፈላቸው ስራቸውን በማከናወን ላይ በነበሩበት ሁኔታ ስለነበርና ስራ በዝቶብናል በሚል ምክንያት ነው የሚል ነበር፤ ፍ/ቤቱም ይህንን ሃቅ ከተገነዘበ እና ተከሳሹም የጎማውን ማራገፍ እስከ ሰኞ ድረስ አቆይቶ አሁንም እንዲያራግፉት ከሳሾችን መጠየቁ በአዋጅ ቁ 337/1996 በአንቀፅ 67 የተመለከቱትን ምክንያቶች እንዳልነበሩ ያሳያል በማለት በአጠቃላይ ከሳሾቹ ስራ ለመሥራት አልፈለጉም ተብሎ በተከሳሽ የተወሰደው ከስራ የማሰናበት ተግባር አግባብነት ያልነበረው በመሆኑ እና ከሳሾቹ በአዋጁ አንቀፅ 10 መሠረት የተቀጠሩ መሆናቸው ማህደራቸው ስለማይገልፅ ተከሳሹ የአዋጁ አንቀፅ 43(4) (ሀ)"ን" መሰረት ያደረገ ካሳ ለከሳሾቹ ሊከፍላቸው ይገባል፤ እንዲሁም የስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜም ክፍያ ጨምሮ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

ከላይ በሰፈረው የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘትም ስር ተከሳሹ ወደ ፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ ወገኖችን ካከራከረ በኋላ መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በኮ.መ/ቁ.60960 በሰጠው ፍርድ ስር ከሳሾቹ በስር ፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ በተከሳሹ ድርጅት ውስጥ በጉልበት ሰራተኛነት ተቀጥረው በመሥራት ላይ እያሉ የኮንትራት ጊዜያቸው ሳያልቅ የስራ ውላቸው እንዳቋረጠባቸው የሚገልፅ በመሆኑና ይህ ደግሞ የስራ ግንኙነቱ ለተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚያሳይ በመሆኑ ሊከፈላቸው የሚገባ ካሳ በአዋጅ ቁ 377/1996 አንቀፅ 43(4)(ሀ) መሰረት ሳይሆን በአንቀፅ 43(4)(ለ) መሰረት ነው፤ የስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያዎች በተመለከተ ግን የስር ፍ/ቤቱ የሰጠው ፍርድ ተገቢ ነው በማለት የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤቱ ውሳኔ አሻሽሏል፡፡

ከላይ በሰፈረው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔም አመልካቹ ቅሬታ በማሳደር ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም በተፃፈ ቅሬታ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም የተጠሪዎቹ የስራ ቅጥር ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው እስከተባለ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 35(2) መሰረት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያው በጊዜያዊ የቅጥር ውላቸው በተስማማነው መሰረት የ15 ቀናት ብቻ እንጂ አንዱ የ2 ወር ደሞዝ አይደለም ተብሎ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎቹም መስከረም 27/2001 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው ከፍተኛው ፍርድ ቤቱ ክርክራችን በአግባቡ ሳያገናዝብ የስራ ግንኙነታችን በአዋጁ አንቀፅ 43(4)(ሀ) ሆኖ እያለ ወደ አንቀፅ 43(4)(ለ) መቀየሩ የህግ ስህተት ነው፤ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ የኮንትራት ሰራተኞች እንደሆንን ቢገልፅም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 35(መ) መሰረት የሙከራ ጊዜያችን ያጠናቀቅን በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያው የሁለት ወራት ደሞዝ ክፍያ ሊሆን ይገባል ተብሎ በከፍተኛው እና በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶቹ የተሰጠው ውሳኔ ህግን ያማከለ በመሆኑ ሊፀና ይገባዋል ብለዋል፡፡

አመልካቹም ህዳር 08/2001 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልሱ ተጠሪዎች ቅጥራችን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 43(4)(ሀ) እንጂ በአንቀፅ 43(4)(ለ) አይደለም በማለት እኔ በአቀረብኩት የሰበር አቤቱታ ሊከራከሩ አይችሉም የራሳቸው የሆነ አቤቱታ ሊያቀርቡበት የሚገባ ነው፤ የኮንትራት ሰራተኞች መሆናቸው አምነው የተከራከሩ በመሆናቸው እና የኮንትራት ሰራተኛ ሊከፈለው የሚገባ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በአዋጁ አንቀፅ 35(2) መሰረት በኮንትራት ውሉ ላይ

የተገለፀው ተብሎ በመደንገጉ በእኛ የኮንትራት ውል ላይ ደግሞ የ15 ቀናት ክፍያ ተብሎ በግልፅ የተቀመጠ በመሆኑ የተጠሪዎቹ መከራከሪያ ነጥብ የህግ ድጋፍ የለውም ብሏል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ በተቀመጠው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ ለተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ስንት ነው የ2 ወር ደሞዝ ወይስ የ15 ቀናት ብቻ የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለው የስራ ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ እንደሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ እንዲሁም እያንዳንዱ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ከፈፀመው ስምምነት መረዳት ይቻላል፤ ሊከፈላቸው የሚገባ ካሳም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 43(4)(ለ) መሠረት ሊሰላ እንደሚገባ ነው፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት መልስ የስራ ግንኙነታችን ለተወሰነ ጊዜ ስላልሆነ ሊከፈለን የሚገባ ካሳም በአዋጁ አንቀፅ 43(4)(ሀ) መሰረት መሆን ይገባል ቢሉም የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ፍርድ በመቃወም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በሌለበት ሁኔታ ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል አከራካሪው ነጥብ ለተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ መጠን በተመለከተ ነው፤ የግራ ቀኙ ወገኖች የስራ ግንኙነት በተወሰነ ጊዜ የተደረገ በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 35(2) መሰረት የሚሰላ ነው፡፡ ይህ አንቀፅም ተዋዋዮቹ ወገኖች በስምምነታቸው ባስቀመጡት መልክ እንደሚከናወን ስለሚገልፅና እያንዳንዱ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በፈፀመው ስምምነት አንቀፅ 3.3 መሠረት የ15 ቀናት ደሞዝ ብቻ እንደሆነ ነው፤ የስምምነታቸው በዚህ መልክ ተገልጾ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የማስጠንቀቂያ ጊዜው ክፍያ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤቱ የወሰነውን የ2 ወር ደሞዝ ተቀብሎ ማለፉ የግራና ቀኙ ወገኖች የስራ ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 60960 መጋቢት 15/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፤ ይፃፍ፡፡
2. በአመልካችና በእያንዳንዱ ተጠሪ መካከል ያለው የስራ ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ በመሆኑ ለእያንዳንዱ ተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 44 እና በስምምነታቸው አንቀፅ 3.3 መሰረት የ15 ቀናት ደሞዝ ብቻ ነው ብለናል፡፡
3. ሚያዝያ 20/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተላለፈው እግድ ተነስቷል፣ ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ያካሄዱትን ክርክር በሚመለከት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
   ክርክሩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ፍርዱ በዛሬው ዕለት 07/05/2001 ዓ.ም በችሎት ተነገረ፡፡

የማይነበብ የአምስት  ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ